www.quatero.net
quatero@gmail.com

# አነስንና ከጌኛ!

ያ ያገሬ ፈረስ እንኳ - መለጎሙ ሲታከተው፤
ጋሪ ጎትቶ ማደሩን - ትከሻው እንብዮ ሲለው፤
መንገድ ለቆ እየታከከ - አግድሞሹን ወደ ገደል፤
የተጓገዞን ምቾት ነስቶ - መመረሩን ያሳውቃል፤

ግና እኛ !
አነስንና ከዚህ ጌኛ!

የሚቻለው ሳይቻለን - የማይቻል ግፍ እየቻልን፤
መቻቻል ነው እንላለን - ያለችሎት እየተቻልን!
እንደ ቃሉ ካልሆነልን - እንደ ትርጉሙ ካልኖርነው፤
አንዱን "ቻ" ከመሃል ገድፈን ቃሉን እንደኛ እናኑረው፡

አዎ እኛ !
አነስንና ከዚህ ጌኛ!

ወኔያችን በፍራት ሞራ - በቂም ተጋርዶ ልባችን፤
በስንት ባለታሪክ ጀግና - የተገነባ ክብር ንደን፤
እንቢኝ ማለቱን ሳንችል - እንሆ እስካሁን አለን!
የግፍ ቀንበር መሸከሙን - ልመድ ጀርባዬ እንዳልን!

መኖር ካልነው ! አዎ አለን!
ከዚህ ከጌኛ እንኳ አንሰን!

አብራራው